19ኛ አመት ቁጥር 10

19th Year No 10

ባህር ዳር ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም

Bahir Dar 27th, April, 2014

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 22.00 Unit Price Birr	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	Contents
ደንብ ቁጥር 122/2006 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	Regulation No.122/2014 The Amhara National Regional State Income Tax Regulation Amendment, Council of Regional Government Regulation

ደንብ ቁጥር 122/2006 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	REGULATION No.122/2014 A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO AMMEND THE INCOME TAX REGULATION OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

በክልሉ ውስጥ የግብር ፍትሀዊነትን ለማስፈን፣ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓትን ለማጎልበትና የግብር ከፋዮችን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት ይቻል ዘንድ የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በስራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አግባብ ያላቸውን ድንጋጌዎች እንደገና የሚያሻሽለውን አዋጅ ቁጥር 213/2006 ዓ.ም ያወጣ በመሆኑ፤

WHEREAS, the Amhara National Regional Council has enacted Proclamation No. 213/2014 amending the relevant provisions of the Income Tax Proclamation No.76/2002 /as amended/ currently in force with a view to bringing about fair taxation, creating favorable conditions for investors, strengthening the system of maintenance of books of account and thereby resolving the problems of good governance pertaining tax payers in the Region;

ይኸው አዋጅ በሚደነግገው መሰረት በስራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 4/1995 ዓ.ም አሻሽሎ አዲሱን ማሻሻያ አዋጅ ገቢራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found necessary to enforce the new amendment Proclamation by equally amending the existing Income Tax Proclamation Implementation Regulation No.4/2003 in accordance with the provision of the said Proclamation thereof;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /58/ ንዑስ አንቀጽ /7/ እና በገቢ ግብር አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 213/2006 ዓ.ም አንቀጽ /2/ ፊደል ተራ ቁጥር /ለ/ ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub-Art. 7 of the Revised National Regional Constitution and Art. /2/, Letter number /B/ of the Income Tax Proclamation Re-amendment Proclamation No. 213/2014, hereby issues this regulation.

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/2006 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This regulating may be cited as "The Amhara National Regional State Income Tax Regulation Amendment, Council of Regional Government Regulation No. 122/2014."

2. ማሻሻያ

በስራ ላይ ያለው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 4/1995 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ ደንብ ተሻሽሏል:-

ከደንቡ አንቀጽ /21/ ንዑስ አንቀፅ /3/ ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀፅ /4/ ተጨምሯል:-

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀፅ /1/ እስከ ንዑስ አንቀፅ /3/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም አዋጁ በሚጠይቀው መሰረት የግዥ ደረሰኝ የማይገኝላቸው አንዳንድ የንግድ ዘርፎች በሚሸጡት ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ በተወሰነው ምጣኔ ወጪያቸው ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ የነዚሁ የንግድ ዘርፎች ማንነት፣ በሚሸጡት እቃ ወይም የአገልግሎት ዋጋ ላይ የሚወሰነው ምጣኔና የወጪው አያያዝ ዝርዝር ባለስልጣኑ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ ይደነግጋል፡፡

3. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር
ነሀሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም.
ገዱ አንዳርጋቸዉ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

2. Amendment

The existing Amhara National Regional State Income Tax Regulation No.4/2003 is hereby amended by this Regulation as follows:

The following new Sub. Art. 4 is added next to Sub. Art. 3 of Art. 21 of the Regulation.

4. Notwithstanding the provisions laid down under Sub-Arts. 1 - 3 of this Article hereof, the expenses of some business sectors whose purchasing vouchers may not have been produced as required by the Proclamation may be computed as per the rate determined on the basis of goods or services to be sold out. The identity of such business sectors, the rate determined on the price of the goods or services to be sold and the detailed computation of the expenses shall be stipulated in a directive to be issued by the authority following this regulation.

3. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at BahirDar
This 27th day of August, 2014
Gedu Andargachew
Head of Government of the Amhara National Regional State